# ጨርቅና ወርቅ ህዝብ

*"ባንዴራው ጨርቅ ነው። ችግሩ ያለው ከጨርቁ ሳይሆን ከጨርቁ በስተጀርባ ያለው ትርጉም ነው"*

*መለስ ዜናዊ*

ህይዎት ምን ጊዜም ቢሆን የተሟላች ሆና አታውቅም። የተሟላች ትሆን ዘንድ ግን የሰው ልጅ ብዙ የፈጠራ ችሎታዎቹን ትግብርት ላይ አውሏል። የሰው ልጅ በፈጠራ ትግብርቱ ዋጋ አልባ ነገሮችን ዋጋ እየሰጠ ህይዎቱን የተሟላ ለማድረግ ብዙ ከጣረባቸው ፈጠራዎቹ መሃል ገንዘብና ጨርቅ ለአብነት የሚጠቀሱ ይሆናሉ። በቅድመ ታሪክ አሞሌ ከምግብ ማጣፈጫነት ያለፈ ዋጋ የነበረው ማዕድን አልነበረም። ዘግይቶ ግን በህበረተሰቡ ክቡር ዋጋ ተሰጥቶት እንደ ገንዘብ አገልግሏል። የገበያ ሸቀጦችም ዋጋቸው በአሞሌ እየተሰላ (እየተተመነ) የንግድ ሸቀጥና የፍጃታ ቁሳቁስ ለመሆን በቅተዋል። ጨርቅም እንደ አሞሌ ገና ከጅምሩ የከበረ ዋጋ አልነበረውም። የሀፍረተ- ስጋ መሸፈኛ፤ የብርድና የሃሩር መከላከያ ከመሆን አልፎ የአንድ ነፃ አገር መለያና መታወቂያ ዓርማ በመሆን የህዝብና የሀገር ፍቅር ከበሬታ ተችሮት ሰንደቅ ዓላማ ሊሆን የበቃው ዘግይቶ ነው። ሰንደቁ አርማነቱ ከታወቀ በኋላ ግን ዜጎች አጥንት ከስከሰውለታል። ደም ረጭተውለታል። ለነጻነት አርማቸው የህይዎት ዋጋ ከፍለው የነጻነት ትውፊቱን ለተተኪው ትውልድ ሲያስረክቡ የታሪክ ሃውልቶች ሆነዋል።

አቶ መለስ ግን ይህን ሀገራዊ ትውፊት ሰንደቅ ዓላማ ከሚጠሉት አማራ ብሔር ጋር አቆራኝተውታል። ለሚጠሉት አማራ ያላቸውን ጥላቻም ለሰንደቁ ሊነፈጉት አልፈለጉም። ቋንቋውን፣ ሰንደቁንና ብሔሩን አንድም ሶስትም አድርገው ሸውራራ ዕይታቸውን አሳርፈውበታል። "ከጨርቁ በስተጀርባ" አለ የሚሉትን "ትምክህት" ለማጥፋት በአማራው ህዝብ ላይ እንደተነሱ ሁሉ በቋንቋውና በሰንደቅ ዓላማው ላይም ዘምተውበታል። ሰንደቁ የነ ስሁል ሚካኤል፣ የነ ራስ አሉላ አባ ነጋና የነ አጼ ዮሐንስ የነጻነት አርማ መሆኑ ለአቶ መለስ አልታያቸውም። በሰንደቁ ውስጥ ጎልቶ የሚታያቸው የሚጠሉት የሚኒሊክ ምስል ብቻ ነው። ለአቶ መለስ በሰንደቁ ውስጥ ጎልቶ የታያቸው ሚኒሊክ ስልጣኑን "ከትግሬ ነጥቆ ለሸዋ" አማራ ሲሰጥ ነው።

አቶ መለስ አጼ ሚኒሊክን ባዩበት ዐይናቸው ሰንደቁንም አዩትና "ትምክህቱን "ገፍፈው ሊያዋርዱት ተነሱ። እርሳቸው እንደ ሚሰማቸውም የዝቅተኝነት ስሜት አማራው ህብረተሰብ ይሰማው ዘንድ ፈለጉና ኩራቱን ገፍፈው የበታችነት ስሜት እንዲያድርበት እኔነታቸውን ሊጭኑበት ዳዳቸው። ከዚሁ ጋርም አያይዘው የኩራቱን ምኩራብ ሰንደቁን ጨርቅ አድርገው ዋጋ ሊነሱት ተንቀሳቀሱ። የክብሩንም ካባ ኢትዮጵያዊነትን ከትምክህት ጋር አዳብለው ሊያጠፉት ዘመቱበት። አማራና የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ከኢትዮጵያዊነት ጋር ተዳምረው አማርኛን ወንጀለኛ እንዲባል በጀማ ፍርድ ቤት ፋይል ከፈቱበት።

**ትምክህት ምንድን ነው?**

ኩራት በራስ የመተማመን እኔነት ነው። በራስ የመተማመን ስሜት የሚወልደው እኔነት ደግሞ ደረት የሚያስነፋ ኩራት እንጂ ራስ የሚያስቀብር የዝቅተኝነት ስሜት አያሳድርም። ለአቶ መለስና ኩባንያው ግን በራስ መተማመን ትምክህት ሊመስል ይችላል። በመለስና ኩባንያው ደም ውስጥ የሚንሸራሸረው የዝቅተኝነት ስሜት የሚፈጥረው የዓመለካከት ዝንፈት የሀገር ፍቅርን ትምክህት አድርጎ ቢመለከተው ማንንም አያስደንቅም።

ሀገራዊ ኩራት ሀረጉ የሚመዘዘው ከቀደምቱ ትውልድ ኢትዮጵያዊነት ስሜት ነው። ስለሆነም አማርኛ ተናጋሪው ህብረተሰብ ኩራቱን የሚቀዳው ከአማራነቱ ምንጭ ሳይሆን ከኢትዮጵያዊነቱ እኔነት መሆኑን ልብ ይሏል። ለአቶ መለስም አልዋጥልህ ያለው ኩራት አማራነት ሳይሆን ኢትዮጵያዊነት ነው።

በኢትዮጵያዊነት የመከየት ስሜት ትምክህት ሊባል ይችላል። መከየቱ የሀገር ፍቅር የሌላቸውን ወገኖች የሚናቁ ካስመሰላቸው ደግሞ ችግሩ የነርሱ እንጂ የሌላው ወገን ሊሆን አይገባውም። በራስ የመተማመን ውስጣዊ ስሜታቸውን አማራው ህብረተሰብ አልገፈፉቸውምና። አማራው ህዝብ በኢትዮጵያዊነቱ መከየቱ፣ ለሰንደቁ ቀናኢ መሆኑና ለሀገሩ ልዕዋላዊነት ዘብ መቆሙ ለባንዳ ልጆች የዐይን ውስጥ ጋሬጣ ሆኖ ሊጋረጥ ይችላል። እናም አቶ መለስ ሲቆረቆራቸው በውስጣቸው የኖረውን የዝቅተኝነት ስሜት( inferiority complex ) የሚጋሩቸው ወገን ፈለጉ። ለዚህም ግብአት "የትግራይን ህዝብ በሳት የተፈተነ ወርቅ ነው። እኔም ከዚህ ህዝብ በመወለዴ እኮራለሁ" ሲሉ ለመናጆ አጬትና ቀሰቀሱት። ጎደሎው ህይዎታቸው የተሟላ ይሆን ዘንድም በሸውራራ አመለካከታቸው ወርቅና ጨርቅ ህዝብ ፈበረኩ።

## የወርቅ ምንነት

ወርቅ የሰው ልጅ ክቡር ዋጋ ከሚሰጣቸው ድንጋዮች አንዱ ነው። ወርቅ ራሱን ችሎ ጌጥ የማይሆን ንጥረ- ነገር ነው። የኔ የሚለው ቀለም የለውም። የኔ የሚለውም ቅርጽ እንዲሁ። ወርቅ ቀለሙንና ቅርጹን የሚመጸወተው ከተጠጋው ኒኬል (Zink)፣ ፕላቲነም (platinum) ፣ ነሃስ (Copper) ፣ ብር (Silver) ፣ ብረት (Iron) ና ካልሲየም (coliseums) ነው። ለዚህም ነው 14ኬ፣ 18ኬ፣20ኬ፣ 21ኬ ወዘተ . . . የሚል ገላጭ ቃል በወርቅ ጌጦች ላይ ተጽፎ የምናየው። ወርቅ ከኒኬልና ከፕላቲነም ጋር ሲደባለቅ ነጭ ወርቅ ይሆናል። ከነሀስ ጋር ሲሆን ቀይ ወርቅ፤ ከብርና ከነሀስ ጋር ሲቀላቀል ቢጫ ወርቅ፤ ከብርና ከካልሲየም ጋር ደግሞ አረንጓዴ ወርቅ ፤ ከብረት ጋር ሲሆን ደግሞ ሰማያዊ ወርቅ ይሆናል። ይህን ዕውነታ አውቀውም ይሁን ሳያውቁ አቶ መለስ ግን የትግራይን ህዝብ ወርቅ ነው ብለውታል።

አቶ መለስ ወርቅ በእሳት እንደሚፈተንም ጨምረው ነግረውናል። የወርቅ ማርከሻው እሳት መሆኑን አስረግጠው። እሳት ውርቅን እንደ ሚያቀልጥ ከተረዳን ዘንድ ዛሬ 24ኬ የወርቅ ጉትቻ፣ 21ኬ የአንገት ሀብል፣ 18ኬ የወርቅ ድኮት 14ኬ የወርቅ ቀለበት ሆነው የሚብረቀረቁ ወርቆች ነገ በዛሬው ቅርጽና ቀለም ለመቀጠላቸው አቶ መለስ የተጨበጠ ዋስትና አላዘጋጀላቸውም። እንዳውም በተጻራሪው ወርቆቹ የሚቀልጡበትን እሳት በላያችው ላይ ኢጋግመው ነበር በሃላፊነት ከመጠየቃቸው በፊት ወደ ላይኛው ዓለም በሽሽት የተሰደዱት።
አቶ መለስን ተከትለው በየ ትልልቅ ከተሞቹ "የአትክልት ወርቅ ቤት"፣ "የብርሃኔ ወርቅ ቤት"፣ "የኪዳኔ ወርቅ ቤቶች" በሚል ስያሜ ተበራክተው የተቋቋሙት የወርቅ ቤቶች ይህ ቀን አልፎ በሌላ ቀን ሲተካ የማን ወርቅ ቤት እንደሚባሉ ሳስበው ራሴን ያመኛል። ያኔ አንጠረኛው ሁሉ ወርቅ በማቅለጥ ባተሌ እንዳይሆንም እፈራለሁ። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሌላም አስፈሪ ነገር ሊኖር ይችላል። ወርቁ ሲቀልጥ አብሮ የሚቀልጥ። ከወርቁ ጋር ወርቁ የተጠጋበት ነሃስ፣ መዳብ፣ ንኬል፣ በረትና ሌላ ሌላውም ንጥረ- ነገር አብሮ መቅለጡ ሲታሰብ ይሰቀጥጣል። ስለሆነም ይህን የማይቀር መጻኢ ዕጣ ፈንታ ታሳቢ አድርጎ ቀኑን ከመግፋት ሳይቀጣጠል በቅጠል እንዲሉ ከወዲሁ ዘላቂ ዘዴ መዘየድ ለውርቁም ሆነ ወርቁን ላስጠጉት ንጥረ- ነገሮች ሳይጠቅም አይቀርም።

ባንድ ወቅት ያነሳውን መልሶ ለመጣል
ቀን ተመላላሽ ነው ፤ ይሄዳል ይመጣል
ስለዚህ ወርቁና ከእርሱም የወገኑ
ዋጋው ሳይወደድ ኋላ ሰቀቀኑ
መበለህ ሳይመሽ ነው ሳይዘነብል ቀኑ

እንዲሉ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች ሳይቃጠል በቅጠል ብለው መላ መምታት ይጠበቅባቸዋል። ለምን? ቢሉ የወርቁ የወደፊት ዕጣ ፈንታ ለወርቁ ጥግ ለሰጡ አካሎችም በተዛማች መትረፉ አይቀርምና።

የትግራይ ህዝብ በሳት የተፈተነ ወርቅ ነው ብለዋል አቶ መልስ። እንደ ርሳቸው አባባል ከሆነ የትግራይ ህዝብ እንደ ወርቅ ራሱን ችሎ መኖር የማይችል ህዝብ ነው ማለት ነው። እንደ ወርቁም የኔነት ማንነቱን የሚመጸወተው ከተጠጋው አካል ነው። እርሳቸው ሊቢያ ሲሄዱ የመናዊ፤ ኤርትራ ሲገቡ ደግሞ ኤርትራዊ እንደ ሆኑት ሁሉ የትግራይ ህዝብም በዝምታው እየነገረን ያለው "የላሙን ልጅ" የሚከተል መሆኑን ነው። የትግራይ ህዝብ መለስን የሚከተል ከሆነ ደግሞ ዕውነትም ወርቅ ነው። ለምን? ቢባል በአቶ መለስ አባባል አለመስማማቱን በተቃውሞ ሲገልጽ አልታየምና። የትግራይ ህዝብ በአቶ መለስ ዐይን ራሱን የማያይ መሆኑን ቢያንስ በውጭ አገር የሚገኘው የትግራይ ማህበረሰብ (በጣት ከሚቆጠሩት በቀር) ከመለስ እንደሚለይ በተቃውሞው ሊያረጋግጥልን ይችል ነበር። ግን አላደረገውም። ይልቁንም የራሱን ቤተክርስቲያንና የራሱን ኮሚኒቲ ማህበር እየመሰረተ ከቀሪው የኢትዮጵያ ህዝብ እየተነጠለ ሲሄዱ ነው የሚስተዋለው። ይህ አቋም ደግሞ እዚያ በዚያው "የላማችን ልጅ" ከሰጠን መታወቂያ ውጭ ሌላ መታወቂያ አያሻንም እንደ ማለት ሊቆጠር ይችላል። የሆነው ሆኖ ግን ኳሷ የምትገኘው አሁንም በትግራይ ሜዳ ነው። የትግራይ ህዝብ በሜዳው የምትገኘውን ኳስ ወደ የትኛው አቅጣጫ እንደሚለጋት ይፋ እስካላደረገ ድረስ ለኢትዮጵያ ህዝብ የጥርጣሬ ምንጭ መሆኑ አልቀረም። እኛም ለትግራይ ህዝብ ብሩህ ብርሁ መንገድ እንዲታየው እየተመኘን ተመላላሹን ቀን በትዕግስት እንጠብቃለን።

ጥር 2007 አብርሃም በየነ
abraham3106@comcast.net